የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፬
አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፰ ቀን ፳፻፮ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 4
ADDIS ABABA 27th December, 2013

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፫፻፪/፳፻፮ ዓ.ም.

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ..........ገጽ ፯ሺ፩፻፳፫

CONTENTS

Regulation No. 302/2013

Ethiopian Electric Power Establishment Council of Ministers Regulation.......... Page 7123

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፪/፳፻፮

## የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይልን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፳፻፩ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፩)(ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፪/፳፻፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. መቋቋም

፩/ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል፡፡

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 302/2013

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN ELECTRIC POWER

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 47(1)(a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Ethiopian Electric Power Establishment Council of Ministers Regulation No. 302/2013".

### 2. Establishment

1/ The Ethiopian Electric Power (hereinafter the "Enterprise") is hereby established as a public enterprise.

2/ The Enterprise shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

## ፫. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን

የውኃ፣ የመስኖ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

## ፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸ ውም ሥፍራ ሊኖረው ይችላል፡፡

## ፭. ዓላማ

ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩/ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ፣ ማስተላለፊያ እና ማከፋፈያ ጣቢያ ግንባታ ሥራዎች የአዋጭነት ጥናት፣ የንድፍ እና ቅየሳ ሥራዎችን ማከናወን፤ እንደአስፈላጊነቱ እነዚህኑ ሥራዎች በኮንሰልታንት ማሰራት፤

፪/ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ፣ ማስተላለፊያ እና ማከፋፈያ ጣቢያ መስመሮችና ጣቢያዎች የግንባታና የማሻሻያ ሥራዎችን ማከናወን፤ እንደአስፈላጊነቱ እነዚህኑ ሥራዎች በሥራ ተቋራጭ ማሠራት፤

፫/ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ እና ማስተላለፊያ መስመሮችን የኦፕሬሽንና ጥገና ሥራዎችን ማከናወን፤

፬/ እንደአስፈላጊነቱ የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ መስመ ሮችን ሊዝ ማድረግ፤

፭/ የኤሌክትሪክ ኃይል በጅምላ መሸጥ፤

፮/ የአገር ዓቀፍ ኤሌክትሪክ ማስፋፊያ ሥራዎችን ማከናወን፤

፯/ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚያወ ጣውን መመሪያና የፖሊሲ አቅጣጫ መሠረት በማድረግ ቦንድ መሸጥና በዋስትና ማስያዝ እና ከአገር ውስጥና ከውጭ የገንዘብ ምንጮች ጋር የብድር ውል መደራደርና መፈራረም፤

፰/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎችን መሥራት፡፡

## ፮. ካፒታል

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ፩፻፴፱ ቢሊዮን ፸፬ ሚሊዮን ፯፻፷፬ሺ ፭፻፷፯ ብር ከ፴፪ ሣንቲም (አንድ መቶ ሰላሣ ዘጠኝ ቢሊዮን ሰባ አራት ሚሊዮን ሰባት መቶ ስልሳ አራት ሺ አምስት መቶ ስልሳ ሰባት ብር ከሰላሳ ሁለት ሣንቲም) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ፴፬ ቢሊዮን ፯፻፷፰ ሚሊዮን ፮፻፺፩ሺ ፩፻፵፩ ብር ከ፹፫ ሣንቲም (ሰላሣ አራት ቢሊዮን ሰባት መቶ ስልሳ ስምንት ሚሊዮን ስድስት መቶ ዘጠና አንድ ሺ አንድ መቶ አርባ አንድ ብር ከሰማንያ ሦስት ሣንቲም በጥሬ ገንዘብ እና በአይነት ተከፍሏል፡፡

## 3. Supervising Authority

The Ministry of Water, Irrigation and Energy shall be the supervising authority of the Enterprise.

## 4. Head Office

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

## 5. Purposes

The purposes for which the Enterprise is established are:

1/ to undertake feasibility studies, design and survey of electricity generation, transmission and substation; to contract out such activities to consultants as required;

2/ to undertake electricity generation, transmission and substation construction and upgrading; to contract out such works to contractors as required;

3/ to handle electricity generation and transmission operational and maintenance activities;

4/ to lease electricity transmission lines as required;

5/ to sell bulk electric power;

6/ to undertake universal electric access works;

7/ in line with directives and policy guidelines issued by the Ministry of Finance and Economic Development, to sell and pledge bonds and to negotiate and sign loan agreements with local and international financial sources;

8/ to undertake any other related activities necessary for the attainment of its purposes.

## 6. Capital

The authorized capital of the Enterprise is Birr 139,074,764,567.32 (One Hundred Thirty Nine Billion Seventy Four Million Seven Hundred Sixty Four Thousand Five Hundred Sixty Seven Birr and Thirty Two Cents ) of which Birr 34,768,691, 141.83 (Thirty Four Billion Seven Hundred Sixty Eight Million Six Hundred Ninety One Thousand One Hundred Forty One Birr and Eighty Three Cents) is paid up in cash and in kind.

## ፯. ኃላፊነት

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

## ፰. ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል።

## ፱. የመብትና ግዴታ መተላለፍ

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፸/፪ሺ፩ እንደገና ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ከኃይል ማመንጫ፣ ማስተላለፊያ እና ማከፋፈያ ጣቢያ ሥራዎቹ ጋር በቀጥታ የተያያዙ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለድርጅቱ ተላልፈዋል።

## ፲. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከህዳር ፴ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፰ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም.

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

## 7. Liability

The Enterprise may not be held liable beyond its total asset.

## 8. Duration

The Enterprise is established for an indefinite duration.

## 9. Transfer of Rights and Obligations

The rights and obligations of the Ethiopian Electric Power Corporation re-established under Council of Ministers Regulation No. 170/2009 which is directly related to its power generation, transmission and substation activities are hereby transferred to the Enterprise.

## 10. Effective Date

This Regulation shall come into force as of the 9th day of December, 2013.

Done at Addis Ababa, this 27th day of December, 2013

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**